

ደያስፖራ የልማት አንዱ ኃይል ነው።



"የኢፌዲሪ የዳያስፖራ ፖሊሲ ዓላማ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከትውልድ አገሩ ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር በአገሩ ልማት፣ሰላምና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ጠቅሞ ትውልድ አገሩንም በመጥቀም በጋራ ለማደግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ መፍጠርና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ማስከበር ነው።"

*ከኢፌዲሪ የዳያስፖራ ፖሊሲ የተወሰደ*

☎ 0115-544600/0115517345 E-Mail:-mfa.community@ethionet.et E-Mail:-diaspora@mfa.gov.et
http://www.ethdiaspora.org.et P.O.Box 393

Printed by Master Printing Press P.L.C.

# ዳያስፖራ ኢንፎርሜ
# Diaspora Informat

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የሚዘጋጅ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም.

**በአስተብኚነት፣ በጉዞ ወኪልነትና በሳፋሪ አገልግሎት የንግድ ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ማሟላት የሚገባቸው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣**

**በውጭ አገር ቆይተው ጠቅልለው የሚመለሱ የዳያስፖራ አባላት የሚያስገቧቸው እቃዎች የጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም፣**

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣**



# ዳያስፖራ ኢንፎርመር
# Diaspora Informer

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሚዘጋጅ

ሚያዚያ 2006 ዓ.ም

# ማውጫ

በአስጐብኝነት፣በአስጐብኝነትና በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጐብኝነትና በሳፋሪ አገልግሎት የንግድ ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች በቅድሚያ ማሟላት የሚገባቸው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ............................................... 3

ወደ ሀገር ቤት የሚገቡ የግል መገልገያ እቃዎች የጉምሩክ ስነስርአት በተመለከተ በዳያስፖራ መታወቅ ስለሚገቡ ጉዳዮች የተዘጋጀ መረጃ ............................................................. 7

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ቤት የሚያስገቧቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ተዘጋጀ መመሪያ .......................................................15





## በአስጐብኝነት፣በአስጐብኝነትና በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጐብኝነትና በሳፋሪ አገልግሎት የንግድ ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች በቅድሚያ ማሟላት የሚገባቸው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

I የማስጐብኘት አገልግሎት

1. ፈቃድን በተመለከተ

1.1 አግባብ ካለው የመንግስት አካል በማስጎብኘት አገልግሎት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።

1.2 አግባብ ካለው የመንግስት አካል የተሰጠ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

2. ተሽከርካሪን በተመለከተ

2.1 ቢያንስ አንድ ከ10-12 መቀመጫ ያለው ሚኒባስ ወይም አንድ 8 መቀመጫ ያለው የመስክ ተሽከርካሪ (4WD Station Wagon ) ወይም አንድ ከ12-45 መቀመጫ ያለው መካከለኛ አውቶብስ ወይም አንድ ቢያንስ 45 መቀመጫ ያለው ትልቅ አውቶብስ ሊኖረው ይገባል፡፡

2.2. ተሽከርካሪው ከተመረተ ከአምስት አመት በላይ ያልበለጠው መሆን ይገባዋል።

2.3 ተሽከርካሪው አጠቃላይ ኢንሹራንስ (Comprehensive Insurance ) የተገባለት መሆን ይገባዋል፡፡

2.4 ተሽከርካሪው በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወቅታዊ እድሳት የተደረገለት መሆን አለበት።

2.5 ለተሽከርካሪው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ለማስጎብኘት አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ማመልከት አለበት።

2.6 በተሽከርካሪው በሮች ላይ የድርጅቱ ዓርማ በሁለት ወገን መለጠፍ ይኖርበታል።

## 3.ተሽከርካሪ የተሳፋሪውን ደህንነት ለመጠበቅ ሊያሟላ የሚገባቸው መስፈርቶች፣

3.1 የተሳፋሪ የደህንነት ቀበቶዎች በአግባቡ የሚሰሩ መሆን አለባቸው፣

3.2 ወቅታዊ እድሳት የተደረገለት የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ የተገጠመለትመሆን አለበት፣

3.3 ቢያንስ ሁለት ቅያሬ ጐማዎች ሊኖሩት ይገባል፣

3.4 በሮቹና መስኮቶቹ በሚገባ የሚከፈቱና የሚዘጉ መሆን ይገባቸዋል፣

3.5 የድንገተኛ አደጋ መከላከያ ሣጥን ከነሙሉ መገልገያ ቁሣቁሶቹ (First aid kit) ሊኖሩት ይገባል፣

3.6 የጐማ ማንሻ ከነሙሉ መገልገያዎቹ ሊኖሩት ይገባል።

## 4. የሰው ሀይልን በተመለከተ

4.1 ባለሀብቱ ወይም የአስጐብኚ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቱሪዝም መስክ (Tour Guide, Tour Operation, Tourism Management) ከታወቀ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋም አግባብ ያለው ዲኘሎማ ወይም ዲግሪ ሊኖረው ይገባል።

4.2 ባለሀብቱ ወይንም የአስብኚ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ከላይ በ4.1 በተመለከተው የትምህርት ዘርፎች የሰለጠነ ካልሆነ ከላይ በተመለከተው መሠረት የሰለጠነ ባለሙያ ስለመቀጠሩ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣

## 5 .የድርጅቱን ቢሮ ወይም ጽ/ቤት በተመለከተ

5.1 ድርጅቱ በግልፅ የሚታወቅ ቢሮ ወይም ፅ/ቤት ሊኖረው ይገባል።

5.2 ድርጅቱ ቢሮው የኪራይ ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት የፀደቀ፣ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የቤት ኪራይ ውል ማስረጃ ወይም ቢሮው የግል ይዞታ ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣





## 6. የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን እና የመገናኛ መሣሪያዎችን አደረጃጀት በተመለከተ

6.1 ቢያንስ አንድ ኮምፒውተር ከነኘሪንተሩ ያለው ፣

6.2 ቢያንስ አንድ ቀጥታ የመስመር ወይም ሽቦ አልባ ስልክ (Wireless telephone)፣ፖስታ ሣጥን ቁጥር፣ ፋክስ፣ የኢ-ሜይል አድራሻ እና የድረ ገጽ (ዌብ ሣይት)ያለው፣

6.3 የጽሕፈት ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ፋይሊንግ ካቢኔት የመሣሰሉት ሊኖረው ይገባል።

6.4 ቢያንስ ሁለት የእንግዳ መቀመጫ ወንበሮች መኖር አለበት፣

## 7. የካምኘ ዕቃዎችን በተመለከተ

7.1 ቢያንስ እያንዳንዳቸው ሁለት ሰዎችን ሊይዙ የሚችሉ 6 የመኝታ ድንኳኖች

7.2 ታጣፊ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ፣

7.3 ታጣፊ አልጋዎች፣ ፍራሾችና ምንጣፎች፣

7.4 የጠረጴዛ ጨርቅ ልብሶች፣

7.5 የምግብ ማብሰያ፣ ማቅረቢያና መመገቢያ ቁሳቁሶች፣

7.6 ምግብ ማብሰያ ምድጃ፣

7.7 አንድ የሻወር ድንኳን (Shower kit) ፣

7.8 ተንቀሣቃሽ ማቀዝቀዣና የበረዶ መያዣ ጆግ/ ፣

7.9 አንድ ተንቀሳቃሽ ጀኔሬተር

7.10 አንድ የእጅ ባትሪ

7.11 አንድ አካፋና አንድ ዶማ

7.12 የእሣት አደጋ መከላከያ መሣሪያ እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና

መስጫ ሣጥን በውስጡ ጥጥ፣ ፋሻ፣ ኘላስተር፣መቀስ አዮዲን ወይም አልኮል ሊኖሩት ይገባዋል ፡፡

## 8. <u>ጥቅል የጉዞና የጉብኝት ኘሮግራሞችን በተመለከተ</u>

8.1 ቢያንስ የዋና ዋና መድረሻዎችን የጉዞ ኘሮግራሞች(Itineraries) የሚያሳይ ፅሁፍ / (Brochure)፣

8.2 ቢያንስ በአንድ የውጭ አገር ቋንቋ የተዘጋጁ የኘሮሞሽን ማቴሪያሎች/ ሕትመቶች ወይም ሲዲዎች፣

## 9. <u>መስፈርቱን ስለማሻሻል</u>

I. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከላይ የተጠቀሰው መስፈርት ሊያሻሽለው ይችላል፣

II. አስጐብኝነትና የጉዞ ውክልና አገልግሎትን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሰው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው መንግስታዊ ተቋም የጉዞ ውክልና የብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆን አለበት፡፡

III. አስጐብኝነትና የየሣፋሪ አገልግሎትን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሰው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው መንግስታዊ ተቋም የአሳዳኝነት ፈቃድ ያለው መሆን አለበት፣

*ከላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላ አስጐብኚ ድርጅት በአስጐብኚነት ኢንቨስትመንት መስክ የተፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር የማስገባት መብት ያለው ሲሆን ጥያቄውን ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አቅርቦ መሥፈርቱን ስለማሟላቱ ተረጋግጦ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎለት የመብቱ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡*





# ወደ ሀገር ቤት የሚገቡ የግል መገልገያ እቃዎች የጉምሩክ ስነስርአት በተመለከተ በዳያስፖራ መታወቅ ስለሚገቡ ጉዳዮች የተዘጋጀ መረጃ

**1.** በውጭ ሀገር የምኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ በሀገሬ ለመኖር ጓዜን ጠቅልዬ ስመለስ ይዤው እንድገባ የሚፈቀድልኝ የግል እና የቤት መገልገያ ዕቃ ዓይነት ምንድን ነው? መጠኑስ?

*<u>መልስ:</u> ተያይዞ በቀረበው ሠንጠረዥ ከተመለከቱት ዕቃዎች ከእያንዳንዳቸው አንድ ወይም እንደዕቃው ባህሪ በሴት አንድ(one in a set) ብቻ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ማስገባት ይችላሉ (ሠንጠረዥ አንድን ይመልከቱ)*

ሠንጠረዥ 1.

የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | የአንዱ CIF ዋጋ በ(USD) | የታሪፍ ቁጥር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሳሎን/የመኝታ ቤት ዕቃዎች | | | | |
| 1. | ቁም ሳጥን | በቁጥር | 131.00 | 94036000 | |
| 2. | ኮንትሮል ብፌ | “ | 131.00 | 94036000 | |
| 3. | አልጋ | “ | 99.00 | 94035000 | |
| 4. | ድሬሲንግ ቴብል | “ | 50.00 | 94035000 | |
| 5. | የሳሎን ጠረጴዛ | “ | 64.00 | 94036000 | |
| 6. | ወንበር | “ | 13.00 | 94038000 | |
| 7. | አረቢያን መጅሊስ | “ | 6.00 | 94018000 | |
| 8. | ሶፋ የሌዘር | በቁጥር | 50.00 | 94018000 | |
| | ሶፋ የጨርቅ | በቁጥር | 47.00 | 94018000 | |
| 9. | ስፕሪንግ ፍራሽ | “ | 47.00 | 94049000 | |
| 10. | የመፅሐፍት መደርደሪያ ሼልፍ | “ | 69.00 | 94036000 | |
| 11. | የመጠጥ ዕቃ ማመላለሻ ጋሪ | “ | 23.00 | 94038000 | |
| 12. | አየር ማስወጫና ሽታ መከላከያ (ፋን) | “ | 57.00 | 84148000 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13. | ወንበር የመናፈሻ | “ | 9.00 | 94035000 | |
| 14. | አልጋ የመናፈሻ | “ | 15.00 | 94035000 | |
| 15. | ድንኳን የመናፈሻ | “ | 27.00 | 63062100 | |
| 16. | ቲቪ ራክ | “ | 37.00 | 94038000 | |
| 17. | ምንጣፍ ሴንቴቲክ >3X4mt | በካ.ሜትር | 1.60 | 57019000 | |
| | ምንጣፍ ጃንያ ስራ >3X4mt | “ | 1.00 | 57019000 | |
| | የወጥ ቤት ዕቃዎች | | | | |
| 18. | የጋዝ ምድጃ ባለ 2 መጣጃ | በቁጥር | 23.00 | 73211100 | |
| | የጋዝ ምድጃ ባለ 4 መጣጃ | “ | 64.00 | 73211100 | |
| | የጋዝ ምድጃ ባለ 5 መጣጃ | “ | 80.00 | 73211100 | |
| 19. | የወጥ ቤት ዕቃ ማጠቢያ ሲንክ | “ | 69.00 | 73249000 | |
| 20. | የአትክልት(የምግብ) መፍጫ ፕሮሰሰር | “ | 25.00 | 85094000 | |
| 21. | የጋዝ ስሊንደር ትልቁ | “ | 30.00 | 73110000 | |
| 22. | ኦቨን(oven) | “ | 61.00 | 85165000 | |
| | የባኞ ቤት ዕቃዎች | | | | |
| 23. | የውሃ ማሞቂያ ግርግዳ ላይ ተለጣፊ | በቁጥር | 25.00 | 85161000 | |
| 24. | የፀጉር መታጠቢያ ገንዳ | “ | 46.00 | 39269090 | |
| 25. | የባኞ ገንዳ | “ | 419.00 | 69109000 | |
| 26. | የመፀዳጃ መቀመጫ ገንዳ | “ | 31.00 | 69109000 | |
| | የስፖርት ዕቃዎች | | | | |
| 27. | የአዋቂ ብስክሌት | በቁጥር | 50.00 | 87120000 | |
| 28. | በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መሮጫ | በቁጥር | 462.00 | 95069100 | |
| 29. | በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት | “ | 289.00 | 9506900 | |
| 30. | የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ በሴት | በሴት | 246.00 | 95064000 | |





| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሙዚቃ መሳሪያ | | | | |
| 31. | ፒያኖ ባለ እግር ለቤት ውስጥ አገልግሎት | በቁጥር | 1222.00 | 92011011 | |
| 32. | የሙዚቃ ኪ ቦርድ መጫወቻ | “ | 119.00 | 42030000 | |
| 33. | ጊታር | “ | 32.00 | 92021000 | |
| | ካሜራ | | | | |
| 34. | ቪዲዮ ካሜራ መካከለኛ | በቁጥር | 330.00 | 85244000 | |
| | ቪዲዮ ካሜራ NVM9500 em | በቁጥር | 330.00 | 85244000 | |
| | ቪዲዮ ካሜራ ትንሹ | “ | 280.00 | 85244000 | |
| | ኤሌክትሮኒክስ | | | | |
| 35. | ቲቪ ከዴክ ጋር 21 ኢንች | በቁጥር | 179.00 | 85281200 | |
| 36. | ደብል ዴክ | “ | 223.00 | 85199300 | |
| 37. | ዴክ ኖርማል | “ | 101.00 | 85211000 | |
| | ቪሲዲ | | 145.00 | 85279020 | |
| | ዲቪዲ | | 156.00 | “ | |
| 38. | ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር | “ | 565.00 | 84714900 | |
| 39. | ላፕቶፕ ኮምፒውተር | “ | 999.00 | 48713000 | |
| 40. | ፕሪንተር ኖርማል | “ | 159.00 | 84714900 | |
| 41. | ፍሪጅ CFC Free/CFC Based | በሊትር | 0.72 | 84182110 84182190 | |
| 42. | የዕቃ ማጠቢያ ማሽን | በኪሎ | 36.00 | 84221100 | |
| 43. | የልብስ ማጠቢያ ማሽን | “ | 36.00 | 84512100 | |
| 44. | ቫኪዩም ክሊነር | በቁጥር | 23.00 | 85091000 | |
| 45. | የቴፕ ስቲከር | በቁጥር | 15.00 | 85182900 | |
| 46. | የመኪና ቴክ ከነስቲከሩ | “ | 30.00 | 85203300 | |
| 47. | ፋክስ | “ | 447.00 | 85172100 | |
| 48. | የፀጉር ካስክ | “ | 60.00 | 85162100 | |
| 49. | የፀጉር ስቲም | “ | 60.00 | 85163300 | |
| 50. | 4 in one fax, printer, copier & scanner | “ | 740.00 | 84716000 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 51. | ስካነር | “ | 75.00 | 84719000 | |
| 52. | የተለያዩ ድሪል 500 ዋት | “ | 32.00 | 85081000 | |
| 53. | ቲቪ. (አንዱን) | | | | |
| | ባለ 14 ኢንች | በቁጥር | 63.00 | 85281200 | |
| | ባለ20 ኢንች | “ | 125.00 | “ | |
| | ባለ21 ኢንች | “ | 170.00 | “ | |
| | ባለ25 ኢንች | “ | 350.00 | “ | |
| | ባለ 29 ኢንች | “ | 735.00 | “ | |
| | ባለ 34 ኢንች | “ | 862.00 | “ | |
| | ባለ 36 ኢንች | “ | 912.00 | “ | |
| | ባለ 43 ኢንች | “ | 1089.00 | “ | |
| | ባለ 50 ኢንች | “ | 1267.00 | “ | |
| 54. | ሲ.ዲ. ማጫወቻ | “ | | | |
| | ባለ 1 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ | በቁጥር | 85.00 | 85279030 | |
| | ባለ 3 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ | “ | 108.00 | 85279030 | |
| | ባለ 5 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ | “ | 123.00 | 85279030 | |
| | ባለ 9 ባለ ሁለት ካሴት ማጫወቻ | “ | 221.00 | 85279030 | |
| | ልዩ ልዩ | | | | |
| 55. | የሳር ማጨጃ አነስተኛ መኪና | በቁጥር | 88.00 | 84331900 | |
| 56. | ጀነሬተር ባለ 4 ኪሎ ዋት | “ | 190.00 | 84051000 | |
| 57. | ሀንድ ቱልስ ሴት አነስተኛ | በሴት | 82.00 | 82059000 | |
| 58. | ሳተላይት ዲሽ | በቁጥር | 410.00 | 85291000 | |
| | ዲሽ ሳህን | “ | 185 | “ | |
| | ሪሲቨርና | “ | 205 | “ | |
| | ኤልኤንቢ. | “ | 20 | “ | |
| 59. | የልብስ ስፌት መኪና ከነ ዲናሞ | “ | 144.00 | 84521000 | |





| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 60. | የመኪና ጎማ ከነቸርኬው | በቁጥር | 27.00 | 40111000 | |
| 61. | ጀልባ እስከ 5 ሰው መያዝ የሚችል | “ | 1356.00 | 89011010 | |
| 62. | ለግል መገልገያ ለሆነ የመኪና መለዋወጫ ሀገር ውስጥ አለመኖሩ ማረጋገጫ ከብቸኛ አስመጪ ካምፓኒው የተሰጠበት እና የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚቀርብበት | | | | |

**2. የግልና የቤት መገልገያ እቃዎቼን ወደ ሀገሬ ለማስገባት ማሟላት ያለብኝ የሰነድ ማስረጃ ምንድን ነው?**

<u>መልስ</u> በነበሩበት ሀገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ የተሰጠዎትን የሰነድ ማስረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሰነድ ማረጋገጫ ክፍል በማረጋገጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ፣

**3. ለግል መገልገያ የሚውል የቤት አውቶሞቢል ወደ ሀገሬ ማስገባት እችላለሁ?**

<u>መልስ</u> አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ በውጭ ሀገር ቆይተው የተመለሱ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ በቀረጥና ታክስ ክፍያ አንድ የቤት አውቶሞቢል ወደ ሀገርዎ ማስገባት ይችላሉ፡፡ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ተሽከርካሪ /የቤት አውቶሞቢል ብቻ /ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችሉ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በውጭ አገር ቆይተው ጠቅልለው የሚመለሱ ብቻ ናቸው፣

**4. በኢትዮጵያ ኢንቨስት ማድረግ እፈልጋለሁ፤ የግልና የቤት መገልገያ ዕቃዎቼን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እችላለሁ?**

<u>መልስ</u> በኢትዮጵያ ከብር 5 ሚሊዮን ያላነሰ ኢንቨስት የሚያደርጉ ከሆነ ጠቅላላ ዋጋቸው ከ10 ሺ የአሜሪካን ዶላር የማይበልጡ የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን በቀረጥ ነጻ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ይችላሉ፡፡ የሚያስገቡት እቃ አይነት ተያይዞ በቀረበው ሠንጠረዥ የተመለከተ

ሲሆን ከእነዚህ ዕቃዎች በነጠላ አንድ ወይም እንደዕቃው ባህሪ በሴት አንድ(one set) ብቻ ማስገባት ይችላሉ፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተሰጠዎትን ማስረጃ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ ይጠበቅበዎታል፡፡

**5. ወደ ሀገረ ያስገባሁት እቃ በጉምሩክ ይፈተሻል?**

**መልስ** ወደ ሀገር ያስገቡትን እቃ የሚያሳይ ዝርዝር እንዳቀረቡ እቃዎት ይፈተሻል፡፡ በተፈቀደልዎ አይነትና መጠን መሰረት የግል መገልገያ እቃ ወደ ሀገርዎ ያስገቡ ለመሆንዎ ለማረጋገጥ ወይም በአይነትም ሆነ በመጠን ያልተፈቀደለዎትን እቃ ወይም የንግድ መጠን የአለው እቃ ወይም በህግ የተከለከለ ወይም ገደብ የተጣለበት እቃ ያልያዙ ለመሆንዎ ለማረጋገጥ ሲባል ፍተሻ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም በተፈቀደልዎ መጠን እና አይነት እቃ ለመያዝዎ የሚጠራጠሩ ወይም ወደ ሀገር ያስገቡትን እቃ አይነትና መጠን በትክክል የማያውቁ ከሆነ ይሄንኑ ፍተሻ ከመካሄዱ አስቀድሞ ለጉምሩክ ማሳወቅ ይጠበቅበዎታል፡፡

**5.1. የንግድ መጠን እና ባህሪ ያለው እቃ ምንድን ነው?**

**መልስ** ‘የንግድ መጠን እና ባህሪ ያለው እቃ’ ከግል ወይም ከቤተሰብ ፍጆታ በላይ የሆነ እና በሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ጥቅም ላይ በመዋል ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል እቃ ነው፡፡ የንግድ መጠን እና ባህሪ ያለው እቃ ወደ ሀገር ማስገባት በህግ የተከለከለ ሲሆን ህጉን ተላልፈው ቢገኙ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበዎታል፡፡ በሚወሰደው እርምጃ መሰረት በእቃው ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ በሁለት እጥፍ ይከፍላሉ፡፡

**5.2. ገደብ የተደረገበት እቃ ምንድን ነው?**

**መልስ** በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 622/2001 መሰረት ገደብ የተደረገበት እቃ ማለት “ ….ስልጣን ባለው አካል በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ ሀገር እንዳይገባ ወይም ከሀገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት እቃ ነው” ገደቡ የተደረገው በተለያዩ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ነው፡፡ ገደብ ከተደረገባቸው ከእነዚህ ምርቶች መካከል በህይወት ያሉ እንስሳት፣ ስጋ፣ የወተት ተዋጽኦ፣አሳና የአሳ ውጤቶች፣ የአበባ ማእድናት ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ እና በሌሎችም የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ገደብ እንዲጣል ካደረጉ ተቋማት መካከል ማዕድን ሚኒስቴር፣ ግብርና ሚኒስቴር፣ የዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ ለምሳሌ የህብረተሰቡን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ ሲባል በህይወት ያሉ እንስሳት ወደ ሀገር እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ግብርና ሚኒስቴር ገደብ ያደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በግብርና ሚኒስቴር እና በሌሎችም ተቋማት የተጣለውን ገደብ የማስፈጸም ተግባር ያከናውናል፡፡

ስለዚህ ገደብ የተደረገበትን እቃ ወደ አገር ካስገቡ ገደቡን ከሚያስከብረው መስሪያ ቤት የተሰጠዎትን ፈቃድ ለጉምሩክ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ፡፡ ገደቡን ከሚያስከብረው መስሪያ ቤት ፈቃድ ይዘው እስኪመጡ እቃው በጉምሩክ ጥበቃና ቁጥጥር ስር ይቆያል፡፡ ገደብ አስከባሪው መስሪያ ቤት የሚሰጠው ፈቃድ በ30 ቀናት ውስጥ ለጉምሩክ ካልቀረበ እቃው ወደ ሀገር እንዳይገባ ወይም ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡ ገደብ የተደረገበት እቃ ወደ መጣበት ሀገር እንዲመለስ በጉምሩክ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ከሀገር ካልወጣ እንደተተወ Abandand እቃ ይቆጠራል፡፡

**5.3. ወደ ሀገር እንዳይገባ የተከለከለ እቃ ምንድን ነው?**

**መልስ** የተከለከለ እቃ ማለት በህግ ወይም ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ወደ አገር እንዳይገባ ወይም ከሀገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ የተከለከለ እቃ ነው፡፡ ከተከለከሉት እቃዎች መካከል ኦፒየም(opium)፣ ጸያፍ ወይም ለመልካም ስነ ምግባር መሸርሸር ምክንያት የሚሆኑ ጹሁፎች፣ ምስሎች፣ ስእላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ፊልሞች፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች፣ የናርኮቲክ እጾች እና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች፣ የዝሆን ጥርስ እና ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ ጌጣጌጦች የሚገኙበት ሲሆን የተከለከሉ እቃዎች ይዞ የተገኘ መንገደኛ እስከ መታሰር የሚያደርስ ቅጣት ሊያጋጥመው ይችላል፡፡

## ማጣቀሻ/reference/


1. የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት ተሰጥቶ የነበረውን መብት የሚገድብ ሚያዚያ 8/2001 በቁጥር /.6/5/1 የወጣ ሰርኩላር፣
2. ተመላሽ ኢትጵያውያን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቧቸው እቃዎች የጉምሩክ ስነ ስርአት አፈጻጸም መመሪያ፣ግንቦት 17/2004 ከወጪ እና ሌሎች እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የተላከ
3. የግል ተሽከርካሪዎች በልዩ መብት በቀረጥና ታክስ ነጻ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ወደ ሀገር ስለሚገቡበት ሁኔታ የተሰጠው መብት ስለመሻሻሉ የወጣ መመሪያ ቁጥር 36/98
4. ክልከላና ገደብ የተደረገባቸው እቃዎች የስራ መመሪያ፣ ቁጥር ሕ/ጥ/ም/040/2001 ቀን22/07/2001
5. ያለውጪ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ እቃዎች የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 66/2004






# የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ቤት የሚያስገቧቸውን ዕቃዎች በተመለከተ የተዘጋጀ መመሪያ

## 1. መግቢያ

ለበጎ አድራጎት ስራ ጉዳይ የሚውሉ እቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ሁኔታ መንግስት አመቻችቷል፡፡ መንግስት በሰጠው መብት ተጠቅመው የበጎ አድራጎት እቃዎችን ወደ ሀገራችን ማስገባት የሚችሉት በሀገራችን የሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ናቸው፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅት ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ለበጎ አድራጎት አላማ ብቻ የተቋቋመና በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ድርጅት ሲሆን የበጎ አድራጎት ማህበር ማለት በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ሆኖ አላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እና ተመሳሳይ ህጋዊ አላማዎችን ለማከናዎን እንዲሁም ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ለመተባበር በአባላቱ ስምምነት የተመሠረተ የሰዎች ስብስብ ማህበር ነው፡፡

## 2. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ወደ ሀገር ቤት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡዋቸው እቃዎች

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚከተሉትን እቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ እነሱም ተሽከርካሪዎች፣ የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ሲሆኑ መለዋወጫዎችን ይጨምራል፡፡ የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ማለት አንድን የልማት ፕሮጀክት ለማስፈፀም ወይም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግሉ ቋሚ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች(accessories) ሲሆኑ አላቂ ዕቃዎችን፣ የፍጆታ ዕቃዎችን፣ የቢሮ መገልገያዎችን፣ የቤት የግንባታ ዕቃዎችን፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የኦዲዮቪዥዋል መሣሪያዎችን አይጨምርም፡፡ ሆኖም ለትምህርት መርጃነት የሚያገለግሉትን እንደ ኦቨርሄድ ፕሮጀክተር (over head projecter)፣ ስላይድ ፕሮጀክተር(slide projecter)ኮምፕዩተር፣ፕሪንተር ሶፍትዌር(Printer software) የማባዣ መሣሪያዎችን ያካትታል፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የልማት ዕቃዎችና መሳሪያዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ እንዲያስገቡ ባለሥልጣኑ ከመፍቀዱ አስቀድሞ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች ለፕሮጀክቱ ያላቸውን አግባብነት ይገመግማል፡፡ እንዲሁም ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተመለከቱትን ሰነዶች አጣርቶ አግባብ ያላቸውን የልማት ዕቃዎችና መሳሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን እቃው ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ላይ

ያልተገለጸ እና ከለጋሾች በበጎ አድራጎት መልክ በተጨማሪ የተገኘ ከሆነ ተገቢ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት እንዲገባ ይፈቅዳል፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እቃዎችን በቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር ለማስገባት የሚከተሉትን ሰነዶች ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ማቅረብ አለባቸው፡፡

3.የቀረጥ እና ተክስ ነፃ መብት ተጠቃሚ ለመሆን በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ሊሟሉ የሚገቡ ሰነዶች

ሠንጠረዥ.2

| ተ.ቀ. | ሊሟሉ የሚገቡ ሰነዶች ዝርዝር | በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊያሟሉት የሚገባ ሰነድ ዝርዝር | ማህበራት ሊያሟሉት የሚገባ ሰነድ ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| 1 | ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግስት መ/ቤት ጋር የተፈረመ የስምምነት ሰነድ | √ | |
| 2 | ስምምነት የተደረሰበት የፕሮጀክት ፖሮፖዛል፣ | √ | |
| 3 | በበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታደሰ የማህበራት ምዝገባ ሰርተፍኬት፣ | √ | √ |
| 4 | የዕቃው ማስጫኛ ሰነድ(bill of lading) በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ | √ | √ |
| 5 | ዕቃው የተገዛበት ደረሰኝ(invoice) በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ | √ | √ |
| 7 | የዕቃው ማሸጊያ ዝርዝር(packing list) በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ | √ | √ |
| 8 | የልማት ዕቃው በእርዳታ የተገኘ ከሆነ የስጦታ ምስክር ወረቀት፣(donation certificate) በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ | √ | √ |
| 9 | የሚመለከተው የመንግስት አካል የፃፈው የትብብር ደብዳቤ፣ | √ | √ |
| 10 | ድርጅቱ/ማህበሩ ከግብርና ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር የተፈራረመው የአጠቃላይ የአተገባበር ስምምነት ሰነድ(General Operational Agreement) ለመጀመሪያ የቀረጥና ታክስ ነፃ ጥያቄ ብቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ | √ | √ |
| 11 | ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳድር ወይም በከተማ አስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግስት መ/ቤት ጋር የተደረሰ የስምምነት ሰነድ፣ | | √ |
| 12 | ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚገባው ዕቃ ለበጎ አድራጎት አላማ ብቻ የሚውል መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ሰነድ፣ | | √ |
| 12 | ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገባው ዕቃ ለበጎ አድራጎት አላማ ብቻ የሚውል መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ሰነድ፣ | | √ |





በሰንጠረዡ በተራ ቀጥር 1(አንድ) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግስት መ/ቤት ጋር የተፈረመ የስምምነት ሰነድ ሳይኖራቸው በተደረገ ጉብኝት ወይም በውጭ አገር ባሉ ለጋሾች በግል ተነሳሽነት የሚደረጉ እርዳታዎች ሲያጋጥሙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዕቃውን በዋስትና በማውጣት ሰነዶቹን ሊያሟሉ ይችላሉ፡፡

4. ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ለአረጋውያን ጉዳተኞች፣ ለህፃናት ማሳደጊያ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ላለ ወገኖችን ለመንከባከብ ሥራ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ለመንከባከብ እና ለመርዳት ተግባር፣ ለቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል(vocational training center) ስለሚካሄዱት የዕርዳታ ተግባር አግባብ ካለው የፌደራል ወይም የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ድጋፍ እስከአገኙ ድረስ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ሚኒባሶችን ወይም አውቶብሶችን ከውጭ ሀገር ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይፈቅዳል፡፡

| በአንድ ማዕከል የታቀፉ የተረጂዎች ብዛት | የተፈቀደው የተሽከርካሪ አይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ15-30 | አንድ ሚኒባስ |
| ከ31-60 | ሁለት ሚኒባስ |
| ከ61-90 | አንድ አውቶቡስ |
| ከ91 በላይ | ሁለት አውቶቡስ |

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ለሚያካሂዷቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ የሞተር ብስክሌቶችን ከውጭ አገር ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ይፈቀዳል፡፡ ድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት አግባብ ካለው የፌደራል ወይም የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ወይም የከተማ አስተዳደር የተሰጣቸውን የድጋፍ ደብዳቤ ሲያቀርቡ ነው፡፡

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎችን መለዋወጫ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ እንደ አግባብነቱ በባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ በባለስልጣኑ የሚፈቀደው የመለዋወጫ እቃ ዋጋ ከዕቃዎቹ ዋጋ ከ15% (አስራ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡ በባለስልጣኑ የተፈቀደው የመለዋወጫ ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ዋናው ዕቃ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን ባለስልጣኑ ከላይ ለተገለፁ ተሽከርካሪዎች እና ሞተር ብስክሌቶች የሚያገለግሉ መለዋወጫዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር እንዲገቡ አይፈቅድም፡፡

ለበጎ አድራጎት ስራ ጉዳይ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር የገባ እቃን በንግድ ሥራ ለተሰማራ መሰል ተቋም አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ሲሆን የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቱን አለአግባብ ተጠቅሞ የተገኘ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አግባብ ባለው ህግ መሠረት በወንጀል ይጠየቃል፡፡

ዋቢ፣ መመሪያ ቁ.79/2005





## ዲያስፖራው ሊሳተፍባቸው የሚችሉ የግንባታ ዘርፍ አማራጮች

በመንገድ ዘርፍ (Road sector)

- Highway Engineering
- Pavement Engineering
- Location Engineering
- Bridge Engineering
- Material Engineering
- Foundation Engineering

በውሃ ዘርፍ (Water sector)

- Irrigation Engineering
- Hydraulics Engineering
- Water Supply & Sewerage Engineering
- Hydrolic Engineering
- Construction Management
- Sanitary engineering

በህንጻ ግንባታ ዘርፍ (Building sector)

- Architecture
- Structural Engineering
- Sanitary Engineering
- Mechanical Engineering
- Quantity Surveying
- Surveying
- Electrical Engineering